| መመልከት ምን አያለሁ? | መተርጎም ምን ማለቱ ነው? | ማዛመድ እንዴት ሊተገበር ይቻላል? |
|---|---|---|

# የገላቲያ ጥናት



**የጥናት ክፍል፡ ገላቲያ ምዕራፍ 4በሙሉ እና 5፡1**

**ርዕስ፡ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል**

በዛሬው ጥናታችን ጳውሎስ አስቀድሞ በእነርሱ ሕይወት አይቶ የነበረውን መለክ ነገር ግን ልዩ ወንጌልን ከመስማታቸው የተነሳ ጠፍቶ የነበረውን መልክ መልሶ ለማምጣት የሚያደርገውን ምጥ እናያለን

በዚህ ክፍል ውስጥ ሕፃን ባሪያና ልጅን በተመለከተ የሚናገራቸውን ቃላት በየሥፍራቸው በመለያየት አስቀምጡ፡፡

| ሕፃን | ባሪያ | ልጅ |
|---|---|---|
| ከጠባቂ በታች | ከህግ በታች | ወራሽ |
| ------ | -------- | አባ አባት |

ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ቃላትን በየቦታቸው እያስገባችሁ ተመልከቱ

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1. በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች ሆናችሁ ተገዛችሁ ሲል ምን ማመልከቱ ነበር? ቁጥር 8
2. የአብርሃም ልጅ መባልና የሳራ ልጅ መሆን ምንድን ነው ልዩነቱ?
3. የባሪያ የልጅ እና የህፃን መገለጫ ምልክቱ ምንድር ነው?
4. በአሁኗ ኢየሩሳሌም እና በሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም መካከል ምን ልዩነት አለ?
5. በቁጥር 3 እና ቁጥር 9 ላይ "መጀመሪያ ትምህርት" የሚለው ምን ለማሳየት ነው?
6. ከቁጥር 13-20 መሰረት ጳውሎስ የገላቲያን ሰዎች የቀድሞ ህይወት በምን መልኩ ያስታውሳል?

**ከግል ሕይወት ጋር ማዛመድ እና መተግበር (Application)**

7. ህፃን ነኝ ወይ ባሪያ ወይስ ልጅ የቱ ይቀድማል? ማን ነኝ?
8. አባ አባት ብሎ መጮህ ምን ማለት ነው ሮሜ 8፡14-17 ?
9. እንደ ልጅ ራሳችንን ከቆጠርን ምን ምን ነገሮችን ወርሰናልን?
10. የክርሰቶስ መልክ እንዴት ተገለጠ እንዴትስ በሰው ላይ ይሳላል የማንንስ መልክ ይዣለሁ?

በዛሬ ጥናት መንፈስ ቅዱስ በተለየ መንገድ አስተምሮኛል የምትሉትን ለቡድናችሁ አካፍሉ፡፡

*መሪ ጥቅስ፡- ልጆቼ ሆይ፥ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል 4፡19*